

Jean de La Fontaine & Lise Lahore

Le corbeau and the Fox – Fable multilingue

Éditions Migrilude 2022

Amharique / አማርኛ

(Couverture)	**ቁራዋና አጅሬ ቀበሮ**
(p. 2)	አንድ ሬይናርድ የተሰኘ ቀበሮ በአንድ ወቅት፣አንዲት ቁራ ቅንጣት አይብ በአፏ ይዛ ስትበር እና በዛፍ ቅርንጫፍ ላይ ስታርፍ ተመለከተ።
(p. 5)	አጅሬ ሬይናርድ "እኔ ቀበሮ እንደመሆኔ ይህ አይብ ለእኔ ነው የሚገባው" አለ። ወደ ዛፉም ስር ተጠጋ።
(p. 7)	"እንደምን ውለሻል እመቤት ቁራ ፣ ዛሬ እንዴት ዉብ ሆነሻል ባክሽ! ላባሽ ምንኛ አንጸባራቂ፣ ዓይኖችሽ እንዴት ብሩህ ናቸው። ሲል ጮክ ብሎ ተናገረ።
(p. 8)	ልክ እንደ መልክሽ ፤ ድምፅሽ ከሌሎች ወፎች ሁሉ እንደሚበልጥ አልጠራጠርም፣
(p. 10)	እንደ ወፎች ንግሥት ሰላምታ እሰጥሽ ዘንድ ፤ እስቲ እባክሽ አንድ ዘፈን ብቻ አሰሚኝ።"
(p. 13)	ቁራዋም ባድናቆቶቹ ቃላት በጣም ደስ አላት። ጭንቅላቷን ወደ ላይ ከፍ አድርጋ የተቻላትን ያህል መቀለጽ ጀመረች። ግን ምን ዋጋ አለው፣ ለመዝፈን አፍዋን በከፈተች ቅጽበት የአይቧ ቅንጣት መሬት ላይ ወደቀች።
(p. 14)	"ይሄ ነው!" አለና የወደቀችውን አይብ ከመሬት አፈፍ አደረጋት። "ይሄን ብቻ ነበር የፈለኩት እቅዴ ተሳክትዋል" አለ እየተፍነከነከ።
(p. 17)	በኩራትና በድል አድራጊነት እየተመለከታት "በአይቡ ምትክ ለወደፊቱ የሚጠቅም አንድ ምክር ልስጥሽ"
(p. 18)	ዝግጁ ነሽ፤ እሺ፡- "እመት ቀበሮ ከንግዲህ ወዲህ አፈ ጮሌ አትመኝ" አላት።

Traduction : Haile Kassa Hailu

Coordination des traductions :
Interbiblio
www.interbiblio.ch
info@interbiblio.ch